# ድንግል ማርያም በቃና ዘገሊላ

ገሊላ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም የትውልድ ሀገርዋ ነው ሀገርዋ
መሆኑንም ወንጌላዊው ሉቃስ በ1ኛ
ም. በ26ኛው ቁጥር ሲገልጽ መል
አኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ከሊላ ከተማ
ስምዋ ማርያም ወደምትባል ወደ አን
ዲት ድንግል ተላከ ሲል ገልጸዋል ፡፡
አንድ ጊዜ በገሊላ አውራጃ ውስጥ
በተለይ ቃና ተብላ በምትታወቀው
መንደር ሰርግ ተደረገ ባለ ሰርጉ ብዙ
ሰዎችን ከመጥራቱም በላይ እመቤ
ታችንንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቷቸው
ነበር ወደ ሰርጉ የታደሙት ሰዎች የተ
ዘጋጀላቸውን መብልና መጠጥ ሲጋብ
ዙ በመካከል የወይን ጠጁ አለቀ የወ
ይን ጠጅ በማለቁም ሰርግ ያደረገው
ሰው የሚይዘውንና የሚጨብጠውን
አጥቶ በከፍተኛ ሐፍረት ተሸፍኖ ሳለ
እመቤታችን ድንግል ማርያም የወይኑን
ማለቅና የሰውየውን ችግር በጸጋ በማወ
ቅዋ ማንም ሳይነግራት ጠጁ እኮ አልቆ
ባቸዋል ፡፡ ስትል ለጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ነገረችው እመቤታችን ማርያም
ጠጅ እኮ አልቋል ማለትዋ እንዲሁ
አልነበረም በሰው ልጅ ላይ በሚደር
ሰው ችግር ምን ያህል እንደምታዝንና
ወሰን የሌለው ርኅራኄ እንደ ምትራራ
ያስገነዝባል ፡፡

እንዲያውም እመቤታችን ድንግል
ማርያም የወይን ጠጅ ማለቁን አይታ ለ
ጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነግራ ውሃ
ውን ወደ ወይን ጠጅ ያስለወጠችውን
አብነት በማድረግ ችግራችንን የምታ
ስወግድልን አማላጃችን ናት ብለን እን
መካባታለን ይሁንእንጂእመቤታችንቅ
ድስትድንግልማርያም ወይንኮአልቆአል
ባለችው ጊዜ ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ
የሰጣት መልስ አንቺ ሴት ካንቺ ጋር
ምን አለኝ ” የሚል ነበር ይህም አባባል
ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ ወይስ እና
ቴ የነገርሽኝን ላልፈጽምልሽ ሰው ሆን
ሁን ማለት ነው የዚህም አይነት አነጋገር
እንግዳ ነገር አይደለም በሁሉም ዘንድ
የተለመደ ነው ፡፡ አንድ ሰው ችግር
ሲያጋጥመውና ችግሩም በዘመድ በወን
ድም የሚወገድና መፍትሔ ያገኛል ብሎ
የሚያምነው ከሆነ ከቅርብ ዘመዱና
ከሚወደው ጓደኛው ዘንድ ሂዶ የደረሰ
በትን ችግር ሲነግራቸው ታድያ ምን
አለው ብለህ ነው ምንስ ያስቸግርሃል
ምንምአይደለም እንደሚሉትና ደርሶ
በት የነበረውን ችግር ተባብረው እንደ
ሚያስወግዱለት ሁሉ እመቤታችንም
የወይን ጠጅ ማለቁን ስትነግረው ካንቺ
ጋር ምን አለኝ ማለቱ ከዚህ የተለየ
አነጋገር አይደለም ፡፡

እመቤታችን ለጌታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ከነገረችው በኋላ ሌላ አልተናገረ
ችም አሳላፊዎቹን በሉ ያዘዛችሁን ሥሩ
አለቻቸው ይኸውም ሳያጐድል ለሁሉ
የሚሰጥ የተጠማውን ሁሉ የሚያረካ
ፍጥረቱን ሁሉ ባለመዘንጋት የሚያስብ
ከማያልቀው ገንዘቡም የሚሰጥ መሆኑን
በማመን ነው ፡፡
አገልጋዮችም እንደታዘዙ በዚያ ሥፍራ
ስድስት የድንጋይ ጋኖች ስለ ነበሩ ጋኖ
ቹን ውኃ ሞሏቸው ከሞሏቸውም
በኋላ በሉ አስቀድማችሁ ለምርፋቁ
አለቃ አቅምሱት አላቸውና የምርፋቁም
አለቃ ያነን ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠ
ውን ውኃ ቀምሶ እጅግ ተደነቀ ነገር ግን
የምርፋቁ አለቃ የወይን ጠጁን ቀምሶ
በጣዕሙና በመዓዛው ቢደነቅም ከየት
እንደመጣ ማን እንደጠመቀው አያው
ቅም ነበር ፡፡

ይህ በእመቤታችን አማላጅነት በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስም ከሃሊነት
ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውንም በመ
ቅመስ የተጠራው ሕዝብና ደቀመዛሙ
ርቱ የክርስቶስን ክብር አይተው አደነቁ
የባሕርይአምላክነቱንምአመኑ፡፡ይህም
ተአምር የመጀመሪያ ተአምር ነበር ፡፡

ይህ ሰርግ ያደረገው ሰው ችግር ያጋጥ
መኛል የሚል በሐሳቡ አልነበረም የሚ
በቃውንም ያህል አዘጋጅቶ ነበርና ነገር
ግን ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንግዶችን
መቀበል አትርሱ በዚህ ምክንያት አንዳ
ንድ ሰዎች መላእክት መሆናቸውን
ሳያውቁ የመላእክትን እንግድነት ተቀ
ብለዋልና ዕብ. 13 ፥ 1 - 2 ሲል እንደ
ተናገረ ይህ በቃናሰርግ ያደረገውም
ሰው ጌታችንና እመቤታችንን ወደ
ሰርጉ የጠራቸው በባህሉ መሠረት እንጂ
የጎደለውን ይሞሉልኛል ጥቂቱንም ያበረ
ክቱልኛል በሚል እምነት አልነበረም
ይሁን እንጂ እመቤታችንና ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስን ባይጠራቸው ኑሮ
ይህን ታላቅ ተአምራት ለማየት ባልበ
ቃም ነበር ፡፡

ዛሬም ክርስቶስን በእምነት የሚጋብዙ
ሁሉ ክርስቶስ ወደ እነርሱ ለመምጣት
ፈቃደኛ ነው “እነሆ እኔ ከደጅ ቆሜ
በር አንኳኳለሁ የሚከፍትልኝ ቢኖር
ወደርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት
እበላለሁ ይላልና ፡፡”

ክንፈ. ርግብ ማርቆስ



ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 52 ጥር 1974

www.ethiopianorthodox.org